

3/9/2019

ሙሐመድ ሙኽታር አሸ-ሺንቂጢ

ኪታር በሐመድ ቢን ኸሊፋ ዩኒቨርሲቲ

የፖለቲካ ስነ-ምግባርና የእምቶች ታሪክ መምህር

# አፍራቢያ Afrabia




ከ1933 እስከ 2014 ድረስ የኖሩት ዐሊ መዝሩዒ የተሰኙ የጥናት ሰው ከፈጠሯቸው የጂኦ-ፖለቲካዊ የገለፃ ቃላት (terminologies) አንዱ ነው። Afrabia

በእንግሊዝኛ ቋንቋ Africa ከሚለው ስም የመጀመሪያ እና Arabia ከሚለው የመጨረሻ ድምፀተ-ቃላት ተዳቅሎ የተፈጠረ ስያሜ ነው። ተመራማሪው እና ዓሊሙ ዐሊ አል-መዝሩዒ በዚህ ስያሜ ሊገልፁ የፈለጉት በአፍሪካ ቀንድ እና በዐረቢያን ፔኒንዙላ መሃል ጥልቅ የሆነውን ጂኦግራፊያዊ፣ ታሪካዊ እና ባህላዊ ቁርኝት እንዲሁም ትስስርን ነው።

‹‹አፍራቢያ›› የሚለው ቃል አውሮፓንና ኤዢያን ከሚሰበስበው ‹‹አውራሲያ›› ከሚለው ጋር ንድፋዊ ተመሳስሎሽ አለው።

ዓሊ መዝሩዒ ኬንያ ሞምባሳ ውስጥ የዘር ግንዱ ከጆርዳን ከሚመዘዝ ኢስላማዊ ቤተሰብ ነው የተወለዱት። ይህ ቤተሰብ ታዲያ ወደ ከዐረባዊና አፍሪካዊ ሁለት ማንነቶች ራሱን ያገኘ ነው። አባታቸው አሚን መዝሩዒ ኬንያ ውስጥ ፈቂህ እና ከትላልቅ ቃዲዎች አንዱ ነበሩ። ዓሊ መዝሩዒ ከጥንታዊ የምዕራቡ ዩኒቨርሲቲዎች ለምሳሌ ማንቺስተር፣ ኮሎምቢያ እና አክስፎርድ ዩኒቨርሲቲዎች ተመርቀዋል። ዩጋንዳ መክሪሪ ዩኒቨርሲቲ አሜሪካ ውስጥ ደግሞ በኒውዮርክና ሚቺጋን ያሉ የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አስተምረዋል። ሃያ አራት መፅሃፍትን አዘጋጅተዋል፣ ስለ አፍሪካና ኢስላማዊ ባህሎች እጅግ የበዙ አርቲክሎችን ፅፈዋል። ብሪታኒያ ውስጥ ለቢቢሲ ‹‹አል-አፋሪቃ›› የተሰኘ ትርጉም ያለው ዶክመንታሪ በማዘጋጀት በደንብ ይታወቁ ነበር።

ከዓሊ መዝሩዒ አፍራቢያ ቃል የተረዳሁት በአፍሪካ ቀንድ እና እኔ እዚህ የዐረብ ቀንድ ብዬ በምጠራው ስፍራ መሃል ያለውን እስትራቴጂያዊ ቁርኝት ቆም ብሎ ማጤንን ነው። ከድሮም በአፍሪካ ክፍለ-አህጉር ደቡብ ምስራቁን ክፍል ሶስት ባህሮች ማለትም ቀይ ባህር፣ የዐረብ ባህርና የህንድ ውቅኖስ የሚገናኙበት ትሪያንግል ቅርፅ ያለውን ክልል ለመግለፅ ዘመናዊ የጂኦ-ፖለቲካ ጥናቶች የአፍሪካ ቀንድ በሚለው ይገልፁታል።

የጂኦ-ፖለቲካ ምሁራን የአፍሪካ ቀንድ የሚለውን ቃል ለሁለት ትርጉሞች ይጠቀሙታል። የመጀመሪያው ትርጉም አራት አገራትን ብቻ የያዘና ጠበብ ያለ ሲሆን እነርሱም ሶማሊያ፣ጅቡቲ፣ኤርትራ እና ኢትዮጵያ ናቸው። ሁለተኛው ትርጉም ደግሞ ሰፊው ሲሆን በደቡብ የኬንያን የባህር ዳርቻ በሰሜን ደግሞ የሱዳንን ባህር ዳርቻ የሚያካልል ነው። በዚህ ትርጉም የአፍሪካ ቀንድ አገራት አራት ብቻ ሳይሆኑ ወደ ስድስት ያድጋሉ። በዚህ ዳሰሳ ግን ለአፍሪካ ቀንድ የመጀመሪያውን ትርጉም እንጠቀማለን። በዚህ አርቲክል ዋናው ጉዳይ በአፍሪካና ዐረብ ቀንድ መሃል ብዙ አጥኚዎች ለሁለቱም ወንዝ ዳር ነዋሪዎች (አፍሪካውያንም ዐረቦችም)፣ ለቀጠናው እንዲሁም እንደምናየው ለተቀረውም ዓለም እጅግ አስፈላጊ ከመሆኑ ጋር ትኩረት ስላልሰጡት የመመሳሰል አዝማማሚያ እና ጥልቅ የሆነ እስትራቴጂያዊ ቁርኝትን ማጉላት ነው።

የዐረብ ቀንድ የሚለውንም ቃል ልክ እንደ አፍሪካ ቀንድ ለሁለት ትርጉሞች መጠቀም ይቻላል። ጠበብ ባለው ትርጉሙ የመንን ብቻ ማለት ሲሆን ሰፋ ባለው ደግሞ ከየመን በተጨማሪ ሳዑዲንና አማንን ይጨምራል። የዐረብ ቀንድ ሰፊውን ትርጉም ከተጠቀምን አንድ ብቻ ሳይሆን ሁለት የዐረብ ቀንዶች ሊሆኑብን ነው። እርሱም አንዱ በደቡብ ምስራቅ

አቅጣጫ በኩል ያለው በኦማን በኩል በሁርሙዝ ባህር ወሽመጥ የሚያቋርጠው የዐረቢያ ቀንድ እና በደቡብ ምዕራብ የመን በኩል የሚያልፈው የባበል መንደብ የባህር ወሽመጥ ነው። ይህ ፅሁፍም ትኩረቱን የሚያደርገው በአፍሪካና ዐረብ ቀንዶች ላይ በባበል መንደብ በኩል ያለውን ይህን ሁለተኛውን ክፍል ነው።



*(ኬንያዊው ሙፈኪር ዓሊ-መዝሩዒ)*

ነገርግን በአፍሪካና ዐረብ ቀንዶች መሃል ወዳለው የቁርኝት መገለጫዎች፣ እነርሱ ላይ ስላለው ቀጠናዊና ዓለማቀፋዊ የቅርምት ሩጫ  በቀጥታ ገብተን ከማውራታችን በፊት ለአንባቢ እስትራቴጂያዊ ጥቆማዎችን በተለይ ደግሞ በአራቱ አገራት ስላሉ ጂኦ-ፖለቲካዊ ትሩፋት እናወሳለን።

1. **ሶማሊያ**፡- በመጪው ጊዜ በቀጠናው ለሚኖራት የላቀ ሚና የሚበጃትን ረጂም የባህር ዳርቻና በር ያላት በአፍሪካ ቀንድ እስትራቴጂ ውስጥ ማዕከል ናት። በርግጥ ይህን ሚና እንዳትወጣ እንቅፋት የሆነው ለዘመናት የተቆራኛት ህገ-መንግስታዊና ያለመረጋጋት ችግር ብቻ ነበር።
2. **ጂቡቲ፡-** ከአፍሪካ ቀንድ አገራት በቆዳ ስፋት በጣም ትንሹዋ ብትሆንም የባበል-መንደብ የባህር ወሽመጥን ባላት ቅርበት የተነሳ ከሌሎቹ በተለየ መልኩ ትቆጣጠራለች።

3. **ኤርትራ፡-** በአፍሪካ ቀንድ ረጂም የባህር ዳርቻን ከያዙት ውስጥ አንዷ ናት። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከኢትዮጵያ ጋር የነበራት ለዓመታት የዘለቀ ችግር እስትራቴጂያዊ አቀማመጧን አናውጦታል።
4. **ኢትዮጵያ፡-** በአፍሪካ ቀንድ ትልቋ፣ በጦር ዝግጅት እና ኢኮኖሚ ጠንካራዋ ናት። ከኤርትራ መገንጠል በኋላ የባህር በር ማጣቷ ግን እጇን አስሯታል። ኃይልና ያላትን ሁሉ በደንብ ፍሬያማ እንዳታደርግ እጀ-ሙቅ ሆኖባታል።

የአፍሪካንና ዐረብ ቀንዶችን የሚያመሳስሏቸውን ጉዳዮች በአራት ነጥቦች ማጠቃለል ይቻላል።

1. ሁለቱም የባበል መንደብን የባህር ወሽመጥ አካለው፣ እርሱም ደግሞ የነዳጅ ዘይት ማሳለጫ እንዲሁም የዓለማቀፍ ንግድ ዝውውር ማለፊያ ነው። ለአፍሪካም ይሁን ዐረብ ባህሮች ዳር ነዋሪዎች ልዩ አስፈላጊነት ሲኖረው ለዓለም አገራትና ባህሩን ለሚጠቀሙትም እንዲሁ ከፍተኛ ሚና አለው።
2. የባህር ዳርቻ ተጠቃሚ አገራት እንዳሉ ሁሉ የባበል-መንደብን የባህር በር የተከለከሉ ግን ደግሞ ስፋት ያላቸው አገራት መኖራቸው። በአፍሪካ ቀንድ በኩል ኢትዮጵያን፣ በዐረብ ቀንድ በኩል ደግሞ ሳዑዲን መጥቀስ ይቻላል።
3. በሁለቱም ቀንዶች በኩል የግዛት መፍረስን አመላካች የሆነ አገር መኖሩ (ሶማሊያና የመን) ሰላምን አናዋጭ ፖለቲካዊ በሽታዎች መኖራቸው ደግሞ ሌላኛው ነው። በድንበሮች አካባቢ የፀነፉ ቡድኖች ሰፊ መንቀሳቀሻ ቦታ አላቸው። የሽብር ቡድኖችና የባህር ላይ ዘረፋዎች የኃይል አንቅስቃሴውን ሁሌም ያሰጉታል።
4. በሁለቱም ቀጠናዎች በአፍሪካዊም ይሁን ዐረባዊ ቅርፁ ማለት በሚቻል መልኩ አብዮትና ተቃራኒው ከውስጣዊና ቀጠናዊ መሳሳቡ ጋር የሌሎች አገራት የሴራ ትግል መጋጋያ መሆኑም ይተቀሳል።

ባለፉት ዓመታት የአፍሪካ ቀንድ አገራት ያቀዷቸውና የጓጉላቸው እስትራቴጂያዊ የሚና መተላለፎች ነበሩ። ለምሳሌ

1. **ጅቡቲ** (ለአሜሪካ፣ ፈረንሳይ፣ ቻይና እና ጣሊያን ..የመሳሰሉ አገራት) ራሷን ለጦር ካምፕነትና ቤዝነት የተከፈተ ምቹ ገቢያ አደረገች። ዋነኛ እስትራቴጂዋ በሁሉም ዓይን ውስጥ መግባትና ከነርሱም መጠቀም እንደሆነ አድርጋ አስመሰለች።
2. **ሶማሊያ** ደግሞ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የእርስበርስ ጦርነት ለመቆጣጠር፣ የመንግስት አልባነትን ችግር ለመፍታት በተለይ የኢማራትን ሰሜናዊ ክፍል ጣልቃ ገብነት ለመቋቋም በሚል ተስፋ ወደ ቱርክና ኳታር ብዙ ተቀራርባለች።

3. **ኤርትራ** በሁሉም ጫፍ መሃል ላይ ሚና ተጫውታለች። ነገርግን እርሷ ኢማራት፣ ሳዑዲና ግብጽ ላሉበት ክበብ በጣም የቀረበች ናት። በቅርብ የተፈታ ይሁን እንጂ ከኢትዮጵያ ጋር ዓመታትን ያስቆጠረ ጠላትነት ነበር።
4. **ኢትዮጵያ** ግን በአፍሪካ ቀንድ ሁሌም የታላቅ ወንድም ሚናን እየተጫወተች ነው። ለዚህ ሚናዋ ደግሞ የአፍሪካ ሕብረት እውቅናን ችሯታል። ነገርግን ቀድመን እንዳወሳነው የባህርበር ማጣቷ ግስጋሴዋን ይገድበዋል።

የተባበሩት ዓረብ ኢሚሬት በአሉታዊ መንገድ አፍሪካ ቀንድ ላይ የበዛ እንቅስቃሴ እንዳላት ይታወቃል። ኢማራት ባለፉት ዓመታት በአፍሪካም ይሁን የዐረብ ባህር ዳርቻዎችን በበላይነት ለመቆጣጠር ተጋግጣለች። በሁለቱ ቀንዶችም ላይ የጦር መሰረቷን በትናለች።

1. ***በዐረብ ቀንድ*** በረጂሙ የየመን ባህር ዳርቻ መሰረቷን የጣለች ሲሆን ከነርሱም ውስጥ ዛሬ ድረስ ያሉት በመከላ፣ ዐደን፣ ጀዚረቱ መይሙን፣ ዙ ባብ፣ እና መኻ ይገኙበታል። የየመን መሬት ክፍል ስለሆነች በፖለቲካው ረገድ ወደ ዐረቡ ቀንድ ነገርግን በጂኦግራፊያዊ አቀማመጧ ወደ አፍሪካ ቀንድ በምትቀርበው በሰቅጣራ ባህረ-ገብም ቤዝ አላት።
2. ***በአፍሪካ ቀንድም*** ደግሞ ኢማራት ብዙ የጦር ቤዝ ያቋቋመች ሲሆን ሶማሊያ ውስጥ በ ቦሳሶ እና በርበራ፤ ኤርትራ ውስጥ ደግሞ የአሰብ ቤዝ ናቸው።

የኢማራት በአፍሪካ ቀንድ መገኘት እስትራቴጂው ሌሎች ጎረቤቶቸንና ወንድሞችን በማግለል ላይ የተቃኘ ነው። የጥቅም ባለቤት፣ የባህሮቹ ላይ ቅፍለቶች  እና የዓለማቀፉ ንግድ ጠበቃ እንደሆነች ለሌላው መግለፅን፤ የባህር ዳርቻዎችንና መተላለፊያዎችን በሙሉ ለመቆጣጥር ጥረት ታደርጋለች። በዚህ የግስጋሴ መንገድ የኢማራት ባለስልጣናት በዐረቡ ቀንድ በየመናውያን ላይ ከአፍሪካ ቀንድ ጋር ማንኛውንም አጋጅ መስሎ በታያቸው ሁሉ ላይ ሰቅጣጭ ድርጊት ከመፈፀም፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ የሞኖፖሊን ልማድ ከማስፋፋት አያወላውሉም። የኢማራት በሁለቱም ቀንዶች ውስጥ መገኘት ለተዋሰኞቹ በቅርብ ጊዜ ሊወገድ የማይችል ጥቁር እንግዳ ነው።

ከዚህ የማይበረታታው የኢማራት አግላይ መገኘት በተቃራኒ መልኩ ቱርክ ከድንበሯ ውጪ ሶማሊያ ላይ ግዙፍ የጦር ቤዝ ገንብታለች። ከኪታር ጋር አንድ ላይ በመሆንም በሶማሊያ ሰብዓዊ ስራዎች እና ሰፊ ኢንቨስትመንት አፍስሰዋል። በዚህ ተግባርም ሁለቱ አገራት ረጂም ጊዜን ከፈጀው የርስበርስ ጦርነትና የሰላም እጦት በኋላ በሰፊው ህዝብና የአገሪቱን ቁስል ለመጠገን በሚሯሯጡ በአብዛሃኛው የፖለቲካ ልሂቃን ዘንድ ቅቡልነተን አግኝተዋል። የቱርክና ኪታር ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የተገነባው የሁሉንም

ተጠቃሚነት ባካተተ የአቃፊነትና ትብብር እይታ ላይ ነው። በሁለቱም ቀንዶች ያሉ አገራትን የህዝቦችን ፖለቲካዊ ምርጫ፣ ወደ ሰላማዊ የዲሞክራሲ ሽግግር ያለውን ጉዞና ፍላጎትም አክባሪዎች ናቸው።

እይታችንን ወደ ትልቁ የአፍሪካ ቀንድ ይዞታ ካሰፋነው ደግሞ ባለፉት ዓመታት ቱርክ በሰዋኪን ደሴት ፕሮጅክቷ በኩል ሱዳን ውስጥ ለመግባት ያደረገቺውን ጥረትም እናገኛለን። ሆኖም ግን ከዑመር አል-በሺር መወገድ በኋላ የኢማራት፣ ሳዑዲና ግብፅ መሪዎች የቱርክን ሱዳን ውስጥ መኖር ስለማይፈልጉት ይመስላል እንደውም ስትራቴጂያዊ ተባባሪያቸውን የአብዮቱ ጎርፍ እንዲወስደው የተውት፣እንዲሁም መፈንቅል አንዲደረግበት የተባበሩት። በወቅቱ የነበረው አለመረጋጋት ሱዳን ውስጥ ለቱርክና ኳታር ኢንቨስትመንት አስቸጋሪ ነበር።

የአፍሪካና ዐረብ ቀንዶች አንዱ በአንዱ ትስስር ከቀን ወደ ቀን በእምነት፣ በታሪክ እና ስረ-መሰረት ገመድ እየተመገበ ስር እየሰደደ ነው። ጂኦግራፊውም ለፖለቲካዊ ኪሳራ ላይጋለጥ በማያዳግም መልኩ የተቆራኘ እየሆነ ነው።

በአፍሪካና ዐረብ ቀንዶች ቀጠና ላይ ስላሉት አገራት ዓላማ በሚከተለው መልኩ አሳጥሮ ማየት ይቻላል።

1. **ኢማራት**፡-በሁለቱም ቀንዶች ላይ በስፋት አለች። አደጋና ጠላትነቷ ለሁሉም ስጋት ነው።
2. **ሳዑዲ**፡- በየመን ጦርነት ወስጥ በግዙፉ አለች። በአፍሪካ ቀንድም ደብዘዝ ያለ ሚና አላት። በሁለቱም ዳርቻዎች ግን ኢማራት ሚናዋን ትሸፍናለች።
3. **ቱርክና ኳታር**፡- ሶማሊያ ውስጥ ጠንከር ባለ መልኩ ሲኖሩ፣ ሱዳን ውስጥ ደግሞ በስሱ አሉ። በበዙ የቀጠናዊ ጉዳዮች ላይ ከሳዑዲና ኢማራት በተቃራኒ ናቸው።
4. **ኢራን**፡- የመን ውስጥ በሁለንተናዋ ሁቲ በተሰኘው እስትራቴጂያዊ ተባባሪዋ በኩል ትገኛለች። የአፍሪካ ቀንድን ፍጅት ለመጠቀም ሁቲዎችን በመሳሪያና ስልጠና ለመርዳትም ትሞክራለች፤ የባበል መንደብን እግር መቆሚያ መንጠቅም ትከጅላለች።

የገልፍ ምስቅልቅል በአፍሪካና ዐረብ ቀንዶችም ላይ ጥላውን ጥሎ ነበር። ይህ ነውጥ የዐረቡ ቀንድ አፍሪካ ቀንድ ላይ ያሉ ችግሮችን ለማቃለል እንዳይረዳ እንቅፋት ሆኖበታል፣ በጣጥሶም ጥሎታል። ዛሬ ላይ የሱማሌዎችና ሌሎች ስደተኞች መሸሺያና መሸሸጊያ የነበረቺው የመን የአፍሪካ ቀንድ ሌላዋ ሸክም ሆናለች። የገልፍ አገራትን ምስቅልቅል

ያመጣው አሰላለፍ ወደ አፍሪካ ቀንድም ራሱን ለጥጧል። ኢማራት፣ ሳዑዲ፣ ግብፅ እና እስራኤልን በአንድ ጎን ስናገኝ፤ ቱርክ፣ ኳታር፣ ሶማሊያ እና በሆነ መልኩ ኢትዮጵያን ደግሞ በአንድ ጎን እናገኛቸዋለን። ዓለማቀፍ ኃይላት ቀጠናውን በሚጠቀሙትና ተልዕኳቸውን በሚፈፅሙበት ልክ በአፍሪካም ይሁን ዐረብ ቀንድ ላይ ለሚከሰቱ ነገሮች ብዙም ራስ ምታታቸው አንዳልሆነ ይታያል።

ከዚህ የሁለት ቀንዶች ቀጠና ላይ ካለው ፉክክር በተጨማሪ ወደ ትብብር ከፍ ያላለ እና ወደ ግጭት ያልወረደ አብሮ የመኗኗር ባህል ግን አለ። ትላልቅ አገራት በአፍሪካ ቀንድ በተለያዩ አገራት ውስጥ የጦር ቤዝ አሏቸው። ከነርሱ ውስጥ አሜሪካ፣ ፈረንሳይ፣ ቻይና፣ ሩሲያ፣ ጃፓን እና ጣሊያን ይጠቀሳሉ። እነዚህ ኃይላት በባበ-ነደብ ባህር በር በኩል የናፍጣ ዘይትንና ዓለማቀፍ ንግዳቸውን ለማሳለጥ የባህር ላይ ዘራፊዎችን ለመዋጋት፣ በጋራ ጥቅማቸው ላይ ተስማምተው አንድ ላይ ይሰራሉ። በነዚህ ጫፎች መሃል ግን ጠንካራ ትብብርን የሚያመላክቱ ነገሮች የሉም።

የአፍሪካና ዐረብ ቀንዶች አንዱ በአንዱ ትስስር ከቀን ወደ ቀን በእምነት፣ በታሪክ እና ስረ-መሰረት ገመድ እየተመገበ ስር እየሰደደ ነው። ጂኦግራፊውም ለፖለቲካዊ ኪሳራ ላይጋለጥ በማያዳግም መልኩ የተቆራኘ እየሆነ ነው። በሁለቱም የአፍሪካና ዐረብ ቀንዶች በኩል ያሉ የረጂም ጊዜ መሰረታዊ ችግሮችን ማሸነፍ የሚቻለው የሁሉንም ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ በሁለቱ መሃል በሚኖር ትብብር ብቻ ነው። ሶማሊያ ውስጥ ከዚህ በፊት እንደተከሰተው የመን እንደ አገር ሙሉ በሙሉ ሳትጠፋና አውዳሚ ኪሳራ ሳይመጣ ጦርነቱን ማስቆም ደግሞ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው። እርስበርሱ የተሳሰረ እንዲሆንና ከአፍሪካ ቀንድ ጋር በአመክንዮ የተመሰረተ ትብብርን ዳግም ማምጣት ይቻል ዘንድ የገልፍን ነውጥም መቋጨት ያሻል። የአፍሪካና የዐረብ ቀንድ ወደ በቅርቡም ይሁን ዘግይቶ ወደ አንድነት ሊያመጣ በሚችል አዲስ እስትራቴጂያዊ እይታ እርስበርስ የሚፈላለጉ ሆነዋል።